First Hijrah Foundation
4324 Georgia Avenue, NW- Washington, DC 20011

**May 9, 2017**

# እስልምና የሰላምና የፍትሕ መንገድ ነው

የእስልምና ሀይማኖት በጽንሰ ሐሳብም ሆነ በተግባራዊ አፈፃፀሙ ሰላማዊና ፍትሐዊ መንገድ መሆኑን ከጅምሩ ለማረጋገጥ እንፈልጋለን። ይህ ሀይማኖት እንደሚያስተምረን ሰዎችን ወደ ሰላም መጋበዝ እንዲሁም ከመጥፎ እንዲርቁ መምከር ነው። እንደሚታወቀው እስልምና ሰዎች ሁሉ እኩል እና ከአንድ ነፍስ የተፈጠሩ መሆናቸውን ያስገነዝበናል። የአላህ መልክተኛ (ሱለሏሁ አለይሂ ወሰለም) ስዎችን አትበድሉ እነሱም እንዳይበድሏችሁ በማለት ሲያስተምሩን እኛ ሙስሊሞች መልካም ስራን በመተግበር ለሌሎች ተምሳሌት እንድንሆን ይጠበቃል።

እስልምናችን ራሳችንንም ሆነ ሌሎችን እንዳንበድል ከትንሽም ሆነ ከትልቅ በደል እንድንርቅ ግዴታ አድርጓል። ትንኮሳን መጥፎ ቅስቀሳን እንዲሁም ፀባጫሪነትን አጥብቆ ይቃወማል። ልዩነትን ለማስተናገድ መቻቻልን እና ማስማማትን ይመክራል። በጦርነት ወቅት እንኳን ያለአግባብ ነፍስ ማጥፋትን ወንጀለኛ ያልሆኑን ዜጎች መዋጋትን ይከለክላል። በስህተት ለጠፋ ህይወት እንኳን የህይወት ካሳ እንዲከፈል ያዛል። የህግ የበላይነት መርህን ያከብራል።

በዚህ መርህ መሰረት ከአምስት ዓመት በፊት የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ሰላማዊ ንቅናቄ ሲጀመር ይዘው የተነሱት መፈክር የኢትዮጵያ መንግስት ህገ መንግስቱን ያክብር ያስከብር የሚል ነበር። ድምጻችን ይሰማ የሚለው መሪ ቃል ሰላማዊ ትግልን ያመላክታል። የወያኔ መንግስት ለፈጸመው የግፍ ግድያ እና የዘር ማጥፋት ዘመቻ የሙስሊሙም ሆነ ሌላው ዜጋ መልስ ሰላማዊ ሰልፍ መውጣት ብቻ ነበር። ይህም ህብረተሰቡ ሰላምና ፍትሕ ፈላጊ መሆኑን ያረጋግጣል። እራሱ ገርፎ እራሱ የሚጮኸው አምባገነኑ የአገራችን የግፍ አስተዳደር እንጂ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ከማንኛውም ወንጀል ነፃ መሆናቸውን በመንግስት የተሰሩት ድራማዎች ሁሉ ከእውነት የራቁ መሆናቸውን ሁሉም የሚያወቀው ጉዳይ ነው። የሙስሊሙን ታማኝነት ጥርጣሬ ውስጥ ለማስገባት እና ለማሸማቀቅ የኢትዮጵያ መንግስት ያላሰለሰ ጥረት አድርጓል።

ኢትዮጵያ ውስጥ የሐይማኖት ግጭት ተስፋፍቷል ለማለት እንዲመቸው እና የተለመደውን የውሸት ውንጀላ ለማራገብ በሶሻል ሚዲያ እና በራዲዮ አገራችን ውስጥ ጅሀድ ሊታወጅብህ ነው የሚል የውሸት ወሬ ያናፍሳል። በተለይ በሰሜን አሜሪካ ውስጥ የሙስሊሙ ትግል ሰላማዊ መሆን የለበትም የሚል እስላማዊ መሰል የትጥቅ ትግልን የሚያበረታታ ራዲዮ እየተሰራጨ ነው። "ሀረከቱል እስላሚያ ዳሩል ሂጅረተይን" የሚባለው ራዲዮ በሳምንት አንድ ቀን በኢንተርኔት እና በሶሻል ሚዲያ እየተላለፈ ነው። የአልቃዒዳን የአይሲስን እና የመሳሰሉትን ወንበዴዎች መንገድ እንደሚከተል ይለፍፋል። ለአገራችን የሚያስፈልጋት ይህ አይነት የግድያ ጥቃት ብቻ ነው በማለት ህዝበ ሙስሊሙን ለማወናበድ እና ወንጀለኞች ለማስባል ሆን ብሎ እየሰበከ ነው።

ሌላ ጅሀዳዊ ሀረካት መሰል ድራማ ለመስራት መንግስት እራሱ ያዘጋጀው ሊሆን እንደሚችል ይገመታል። የኛ መልስ ትግላችን አሁንም ቢሆን ሰላማዊ እና ፍትሓዊ ነው። ማንኛውንም ዜጋ ከዚህ አይነት ጽንፈኛ ፕሮፓጋንዳ እንዲጠነቀቅ እንዲርቅና በማንኛውም መንገድ እንዳይሳተፍ አጥብቀን እንመክራለን።

አላሁ አክበር

ፈርስት ሂጅራ ፋውንዴሽን